# ያ ትውልድ

## የሀዘን መግለጫ (አምባሳደር እምሩ ዘለቀ)




ወጣት እምሩ ዘለቀ
Young Imiru Zeleke

አምባሳደር እምሩ ዘለቀ

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1923 ከአባታቸው በጅሮንድ ዘለቀ አግደውና ከእናታቸው ከወ/ሮ አዛለች ጎበና አዲስ አበባ ኢትዮጵያ የተወለዱት አምባሳደር እምሩ ዘለቀ October 21, 2022 ማረፋቸውን ስንሰማ ጥልቅ ሀዘን ተሰምቶናል። ሀገር ወዳዱ አምባሳደር እምሩ በህይወት ዘመናቸው ለሀገራቸው ኢትዮጵያ ሳይታክቱ ድምጻቸውን ያሰሙ ብርቅዬ ኢትዮጵያዊ ነበሩ። እድሜያቸውን ስለ ሀገር እየተቆረቆሩ ድምጻቸውን ከማሰማት አልፈው የራሳቸውን ጥረት በማድረግ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን በማድረጋቸው ይታወቃሉ። ፌስ ቡክ በመሳሰሉ ማህበራዊ ሚድያ ጭምር ስለ ሀገር የሚከትቡና ሚሞግቱ የኢትዮጵያ አባት በማጣታችን አዝነናል። በእድሜ ተመክሯቸው አበርክተው ካለፉት መጻሕፍትና አነስተኛ ወቅታዊ መጣጥፍ ትውልድ ትምህርት ይቀስምበት ዘንድ አስቀምጠውልን ያረፉ የዕድሜ ባለጸጋ ናቸው።

የዘጠና ዘጠኝ ዓመቱ የዕድሜ ባለጸጋ አምባሳደር እምሩ ዘለቀ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን በጀርመን በጋናና በእስካንዴንቪያ ሀገራት አምባሳደር ሁነው ሰርተዋል። በሁናይትድ ስቴት ዎል እስትሬት በኬሚካል ባንክ ውስጥ የአፍሪካ ምክትል ፕሬዘደንትና የልዩ ልዩ ኩባንያዎች የንግድ አማካሪም ሁነው አገልግለዋል። የካቲት 12 ጣሊያን ከ30ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያንን በጨፈጨፈበት ወቅት ሁኔታውን በዓይን የተመለከቱ እና ስለሁኔታውም የጻፉ ኢትዮጵያዊ ናቸው።

<<ያ ትውልድ ተቋም>> በአምባሳደር እምሩ ዘለቀ ከዚህ ዓለም መለየት የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን እየገለጽን ለቤተሰቦቻቸው፣ ለዘመድ አዝማድና ወዳጆቻቸው በሙሉ እግዚያብሔር ብርታትና መጽናናትን ይሰጥልን ዘንድ እንመኛለን። ረዥም የእድሜ ተመክሮ ከአላቸው አምባሳደር እምሩ ብዙ መታወቅ ያለባቸውና ምርምር ሊደረግባቸው የሚገቡ ሥራዎቻቸውን በመመርከዝ ቀጣይ ትውልድ ጥናትና ምርምር እንደሚያደርጉበት ተስፋ አለን።

<<ያ ትውልድ ተቋም>> የቀደምት ትውልድ ታሪኮችን መዘገብ አስተማሪነቱን በመገንዘብ አምባሳደር እምሩ በተለይ በውጭው ዓለም በነበሩበት የሕይወት ዘመናቸው ከተለያዩ ሚድያዎች ጋር ከአደረጓቸው ውይይቶች እጅግ ጥቂቱን ለትውስታ ከታች አስቀምጠናቸዋል። በተለይ አማራው ይደራጅ ብለው “ሞረሽ” የሚል እንቅስቃሴ በጀመሩ ጊዜ የገጠማቸውን እና ስለ አማራ መደራጀት የአቀረቡትን ጽሁፍ አስመልክቶ ከስድስት ዓመት በፊት በኢሳት ቲቪ ያደረጉትን ውይይት በቀጣዩ መጠቆሚያ አድምጡት።

ESAT January 9, 2016 https://youtu.be/Tus0n9OYQMA

ESAT August 16, 2018 https://youtu.be/hJwcx0zvCwE

**በሸገር** FM March 25, 2019 https://youtu.be/hJwcx0zvCwE

**ያ ትውልድ ተቋም ጥቅምት** 19 **ቀን** 2015 **ዓ.ም**. (October 29, 2022)